
# Legacy International Spiritual Ministry 2023 GC Annual Summary Report




**Legacy International Spiritual Ministry**
**c/o P.O.Box 17979**
**Cell # 251 930 651943**
**Act: #: Berhan Bank 2600010008458; Awash Bank 013521121036500; CBE 1000312358337**
**Addis Ababa, Ethiopia**


***ለዉድ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ደጋፊዎች!***

***ጉዳዩ፡*** **እአአ 2023 የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት ዓመታዊ ሪፖርት ባጭሩ**

ሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2017 በይፋ ሥራዉን ከጀመረ ስባተኛ ዓመቱን አጠቃልሎ ስምንተኛዉን ተያይዟል። ሰባተኛዉን ዓመት ሲያጠቃልል በሥራ አመራር ቦርዱና በጠቅላላ ጉባዔ እአአ የ2023 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴና የኦዲት ሪፖርትን በማድመጥና በማጽደቅ ነበር። የበጎ ፈቃደኞች (በተለይ ወጣት አሠልጣኞች)፣ በጊዜያቸው፣ በዕውቀታቸውና በሀብታቸው ከአገልግሎቱ ጎን የመቆም ሂደት አሁንም ቀጥሏል። የአገልግሎቱ አንኳር ተግባር የሆነዉ ማለትም ለሚመለከታቸዉ ተደራሾች በተለያዩ አካባቢዎች የግንባር ሥልጠናን የመስጠት ሥራ በሰባተኛዉ ዓመት ከታቀደዉ አንጻር ሲታይ የ186 % ክንዉን ዉጤት ታይቶበታል። ይህ ዉጤት ካለፈዉ ዓመት ጋር ሰወዳደር ዘቅተኛ ቢመስልም ከተቀደዉ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ነዉ፣ በመሆኑም፣ እግዚአብሔር ስላበዛልን ፀጋ እናመሰግነዋለን። በዚህ በሰባተኛ ዓመት ማጠቃለያ ሁለት ተርም ያገለገሉ ሶስ፤ቦርድ አባላት ከአገልግሎት አርፈዉ በሌሎች ተተክተዋል። በትዕግሥትና በትጋት ሳያቋርጡ ስድስት ዓመታት ስላገለገሉ ጌታ ይባርካቸዉ። ሌላዉ ሰባተኛ ዓመቱን ልዩ የሚያደርገዉ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት **ሰንበት** ላይ መሆኑ ነበር፣ ለዚህም ጌታ ይባረክ።

## ክፍል አንድ - የጥምረት ጥምረት መፍጠር

### 1.1 የልጆች አገልግሎቶች ጥምረት ጥምረት (CAG & VAE)* መሪዎች

በወርልድ ቪዥን ድጋፍ የሁለቱ ጥምረቶች መረብ በደብረ ዘይት/



## ክፍል ሁለት - በእግዚአብሔር መንገድ መምራት (Guidance)

**እአአ 2023 እሁድ አምልኮ ጨምሮ በግንባር የተሰጡ የወጣቶች፣ ወላጆችና መሪዎች/አገልጋዮች ሥልጠናዎች;**

### 2.1 የወጣቶች ግንባር ሥልጠና

**2.1.1** የወጣቶች፣ የየዕለት ግል ጥሞና ጊዜ ከጌታ ጋር ስልጠና መሠረታዊ ዳሰሳና ትንተናዎች እአአ 2023 በተወሰኑ የስልጠና ጣቢያዎች- ተደርገዋል፣ ለወጣቶች ሥልጠናዉን ሲወስዱ የተደረገዉ መሠረታዊ ቅድመ ሥልጠና ዳሰሳ፣ ድህረ ሥልጠና ግብረ መልስ እና በጥቅሉ የተደረገዉ ትንተና ወጣቶች ያደረጉትን ዉሳኔ ሊገልጽ የሚችል መረጃ ነዉ።

በዘሁም መሠረት የተወሰኑ ጣቢዎችን ሥራ ለመተንተን በተደረገዉ ጥረት የሚከተሉት፣ ማለት፣ እአአ 2023 የዉሳኔ ለዉጥ መረጃዎች ተገኝተዋል።

በአምቦ ቦሌ ሙሉ ወንጌል 17%፣ በአረርቲ ሙሉ ወንጌልና አዲስ ኪዳን ቤተ ክርሰቲያን 35%፣ አረካ ሙሉ ወንጌል 0%፣ ተፍኪ ሙሉ ወንጌል 3%፣ ቡታጅራ ሙሉ ወንጌል 39% ናቸዉ።

* **CAG = Christian Alliance for Generation; VAE)= Voice Alliance Ethiopia**

ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነ ዉ።

**2.1.2 ለወጣቶች - ወጣትነት፣ ተግዳሮቶችና መፍትሔ ሃሳቦች፣ በአእምሮ መንፈስ መታደስ (5ቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች ላይ ተመሥርቶ) ፣ የየዕለት ግል ጥሞና ጊዜ ከጌታ ጋር**

**ሀ. በአምቦ በሌ ሙሉ ወንጌል የወጣቶች** ሥልጠና፡- የካቲት 25፣ 2015 (March 4, 2023) የተካሄደ ሲሆን የተካፈሉት፣ ወጣቶች በከፍተኛዉ ቁጥር **278** ናቸዉ፣



**አምቦ በሌ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን የወጣቶች ሥልጠና ተሳታፊዎች**

**ሐ. በአረካ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን ሚያዝያ 12-15፣ 2015 ዓ.ም.** (April 20 - 23, 2023) በተካሄደዉ ሥልጠና፣ የተካፈሉ ወጣቶች **ቁጥር 99 ነበር።**



**አረካ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያ የወጣቶች ሥልጠና ተካፋዮች**

**[illegible]. [illegible] (illegible)** [illegible] 22-24[illegible] 2015 (March 31 – April 2, 2023) [illegible] 28 [illegible]



**ከአረርቲ ሙሉ ወንጌል እና አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ሥልጠና ተካፋዮች**

**መ. ተፍኪ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን** ከመስከረም 15-17፣ 2015 (September 26-28፣ 2023) በተካሄደዉ ሙሉ ፓኬጅ ሥልጠና የተካፈሉት ወጣቶች **344** ናቸዉ።



**ተፍኪ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን የወጣቶች ሥልጠና ተካፋዮች**

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።**

**ሠ. ቡታጅራ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል** ቤተ ክርስቲያን ከህዳር 5—8፣ 2015 (November 15-18፣ 2023)፤ በተካሄደዉ ሥልጠና፣ የተካፈሉት ወጣቶች በከፍተኛዉ ቁጥር **61** ናቸዉ።



**ቡታጅራ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ሥልጠና ተካፋዮች**



**አምቦ ቦሌ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን የወላጆች ሥልጠና ተሳታፊዎች**

**ሐ.ከአረካ ሙሉ ወንጌል አማኞች** ቤተክርስቲያን ጋር በመተባበር ሚያዝያ 12-15፣ 2015 ዓ.ም. (April 20 - 23, 2023) ሲካሄድ፣ የተካፈሉት ወላጆች ቁጥር **72** ነበር።



**አረካ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወላጆች ሥልጠና ተካፋዮች**

**2.1.3 ከወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ለወላጆች በግንባር የተሰጡ ሥልጠናዎች፤**

**ሀ. አምቦ ቦሌ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን** ከየካቲት 23-25 2015 ዓ.ም.(March 2 - 4, 2023) በዓልና ሥልጠና ተካሂዷል። በልዩ የባለትዳሮች ምሥጋና በዓል ላይ **286** ሰዎች፣ በወላጆች ሥልጠና ላይ ደግሞ 149 ሰዎች የተካፈሉ ሲሆኑ በከፍተኛ ቁጥር ድምር **435** ሰዎች ናቸዉ።



**አምቦ ቦሌ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን የባለትዳሮች በዓል ተሳታፊዎች**

**ለ. ከአረርቲ ሙሉ ወንጌል** (ግንባር ቀደም አስተባባሪ) እና **ከአረርቲ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን** ጋር በመተባበር መጋቢት 22-24፣ 2015 (March 31 – April 2, 2023) በተዘጋጀዉ ሥልጠና የተካፈሉት ወላጆች ቁጥር **39 ነበር።**



**ከአረርቲ ሙሉ ወንጌል እና አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ወላጆች ሥልጠና ተካፋዮች**

**መ. በማራናታ የኢትዮጵያዉያን ቤ/ክ ጋር በመተባበር** ሁለት ጊዜ በተከታታይ **በሳንዲያጎ ካሊፎርኒያ (USA)** በተደረገዉ **የወላጆች ሥልጠና** በድምሩ የተካፈሉት **63** ናቸዉ።

**ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።**

**ኢየሱስ ጌታ ነዉ።**

**2.1.3 ሠ. ከተፍኪ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ጋር በመተባበር** መስከረም 15-17፣ 2015 (September 26-28፣ 2023) በተካሄደዉ ሥልጠና የተካፈሉት ወላጆች ቁጥር **175 ነበር።**





**ተፍኪ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ወላጆች ሥልጠና ተካፋዮች**

**2.1.4 ከወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ለ**መሪዎችና አገልጋዮች **በግንባር የተሰጡ ሥልጠናዎች፤**

**ሀ. ከተፍኪ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ጋር በመተባበር** የተካሄደዉ ሙሉ ፓኬጅ ሥልጠና ከመስከረም 15-17፣ 2015 (September 26-28፣ 2023) ሲሆን፣ ሥልጠናዉን የተካፈሉት መሪዎችና አገልጋዮች ቁጥር **39 ነበር።**

**2.1.3 ረ. ቡታጅራ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል** ቤተ ክርስቲያን ከህዳር 5—8፣ 2015 (November 15-18፣ 2023)፤ በተካሄደዉ ሥልጠና፣ የተካፈሉት ወላጆች በከፍተኛዉ ቁጥር **49** ነዉ።



**ቡታጅራ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን የወላጆች ሥልጠና ተካፋዮች**

**ለ. ከቡታጅራ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን** ጋር በመተባበር በተሰጠዉ ሥልጠና የተካፈሉት መሪዎችና አገልጋዮች **ቁጥር 71** ነበር።



**የቡታጅራ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን የመሪዎችና አገልጋዮች ሥልጠና ተካፋዮች፣**

**ፎቶ**

## ክፍል ሶስት—የቀድሞ ሥልጠና ጣቢያዎች ጉብኝትና በጥቅሉ የተገኘዉ ዉጤት

**3.1 ደብረ ዘይት ለምለም መካነ የሱስ** አስተባባሪነት፣**ቀደም ብሎ የ**ወላጆች ሥልጠና የተካሄደዉ ሚያዝያ 23፣ 2011 የነበረ ሲሆን፣ ጉብኘት የተደረገዉ ደግሞ ህዳር 22፣ 2016 (December 2, 2023) ነበር። የጉብኙቱ ዓላማ - ቀድሞ ስለተሰጠዉ ሥልጠና ግብረ መልስ ለማግኘትና በወቅቱ የትዉልዶች ተግዳሮቶች ላይ ሥልጠና ለመስጠት ነዉ። በጉብኙቱ ፕሮግራሙም ላይ የተሳተፉት **21 ሰዎች** ሲሆኑ፣ የቀደመዉን ሥልጠና ተካፍለዉ የነበሩ ወላጆች 5 ናቸዉ። በተጨማሪም በቀጣይነት ትዉልድን ለማስመለጥ የሚረዳ ለሶስት ወር የሚያገለግል የወላጅነት መጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ማቴሪያል ተበርክቷል። ከግብረ መልሱም በቀደመዉ ሆነ በቀኑ በተደረገዉ ሥልጠና የጠቀማቸዉን፣ የነበሩት ጠንካራና ደካማ ነጥቦች፣ እንዲሁም ሊሻሻሉ የሚገባቸዉና ለሌጋሲ አገልግሎት ግብዓት የሚሆኑ ገንቢ ሃሳቦችም ተሰብስበዉ ለመረጃነት ተይዘዋል።






**ደብረ ዘይት ለምለም መካነ የሱስ ማህበረ ምዕመናን የቀድሞ ሥልጠና ጉብኝት ተካፋዮች**

**3.2 በሀረር አካዳሚ ሙሉ ወንጌል ቤተክርሰቲያን አስተባባሪነት ቀደም ብሎ ሙሉ ፓኬጅ** ሥልጠና **(**ወላጆች፣ ወጣቶች፣ መሪዎች) የተካሄደዉ ነሐሴ 2010 ዓም. (August 2018) ሲሆን፣ ጉብኘት የተደረገዉ ደግሞ ታህሳስ 13፣ 2016 (December 23, 2023) ነበር። የጉብኙቱ ዓላማ - ቀድሞ ስለተሰጠዉ ሥልጠና ግብረ መልስ ለማግኘትና በወቅቱ የትዉልዶች ተግዳሮቶች ላይ ሥልጠና ለመስጠት ነዉ። በጉብኙቱ ፕሮግራም ላይ የተሳተፉት 6**2 ሰዎች** ሲሆኑ፣ የቀደመዉን ሙሉ ፓኬጅ ሥልጠና ተካፍለዉ የነበሩ ወላጆች፣ ወጣቶችና መሪዎች **11** ናቸዉ። በተጨማሪም በቀጣይነት ትዉልድን ለማስመለጥ የሚረዳ ለሶስት ወር የሚያገለግል የወላጅነት መጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ማቴሪያል ተበርክቷል። ከግብረ መልሱም፣ በቀደመዉ ሆነ በቀኑ በተደረገዉ ሥልጠና የጠቀማቸዉን፣ የነበሩት ጠንካራና ደካማ ነጥቦች፣ እንዲሁም ሊሻሻሉ የሚገባቸዉና ለሌጋሲ አገልግሎት ግብዓት የሚሆኑ ገንቢ ሃሳቦችም ተሰብስበዉ ለመረጃነት ተይዘዋል።





**በሀረር አካዳሚ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ ሥልጠና ጉብኝት ተካፋዮች**

**ማስታወሻ፣** በሁሉም 6 ጣቢያዎች በተደረገዉ ሥልጠና የተካፋዮች **ቁጥር 1753** ሲሆን በቀድሞ ሥልጠና ጉብኝት ዉቅት በ2 ጣቢዎች የተገኙት **በድምሩ 83** በመሆናቸዉ፣ በ8 ጣቢዎች የነበሩ ተሳፊዎች ድምር **1836** ነዉ።

## ክፍል አራት—በእሁድ አምልኮ ላይ በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጪ የተደረጉ እንቅስቀሴዎች

**4.1 በሀገር ዉስጥ** በግምት የተካፈሉት ቁጥር፣ ሀ. አምቦ በሌ ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ(1500 ሰዎች) ለ. አረርቲ ሙሉ ወንጌልና አዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት(250 ሰዎች) ሐ. አረካ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን, (1650 ሰዎች)፣ በቡታጅራ ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል (600 ሰዎች)፣ በሀረር አካዳሚ ሙሉ ወንጌል (600 ሰዎች) ነበሩ።

**4.2 ከሀገር ዉጭ፣** በግምት የተካፈሉት ቁጥር ሀ. የኢትዮጵያዉያን ህብረት ቤ/ክ በፎንታና ሎስ አንጄሌስ (30 ሰዎች)፣ ለ. አምባሳደርስ የኢትዮጵያዉያን ህብረት ቤ/ክ በሲያትል (30 ሰዎች)፣ ሐ. አዲስ ኪዳን የኢትዮጵያዉያን ህብረት ቤ/ክ በሲያትል (15 ሰዎች)፣ መ. ማራናታ የኢትዮጵያዉያን ክርስቲያኖች ህብረት በሳንዲያጎ (150 ሰዎች) ነበሩ።

# ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነዉ።

### እአአ 2023 የሁሉም ሥልጠናዎችና እሁድ አገልግሎት ማጠቃለያ

በጥቅሉ በ2023 በጀት ዓመት **110** መሪዎችና አገልጋዮች፣ **810** ወጣቶች፣ በወላጅነት ሥልጠና ላይ **783** ተሳታፊዎች ሥልጠና እንደ ወሰዱ፣ በድምሩ በተለያዩ 6 ጣቢያዎች **1753** ሠልጣኝ ተሳታፊዎች እንደነበሩና ይህ ለዓመቱ ከታቀደዉ **1090** ጋር ሲነጻጸር **161%** ክንዉን ያሳያል። በዓመቱ በእሁድ አምልኮ ላይ 2500 ታቅዶ በዓመቱ የሌጋሲን መልእክት የሰሙ በግምት **4825** ሲሆኑ በጠቅላላዉ 3560 ታቅዶ **6661** ሰዎች እንደተደረሱ ነዉ። ይህም በጥቅሉ 186**%** ነዉ። ስለዚህም ቸሩ እግዚአብሔር ምሥጋና ይድረሰዉ። አሜ! አሜን! አሜን!

## ክፍል አምስት - የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎቶች

**5.1 በዌብሳይት ፌስቡክ ገጽ በሶሻል ሚዲያ እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶች (**እአአ ጁላይ 28 እስከ ኖቬምበር 8፣ 2022 )

ሶስት የተለጠፉ የሌጋሲ መልእክት አዘል ፅሁፎች፣ ማለትም፣ የምሥጋና ጉልበት (በ123 ሰዎች)፣ ቤተሰብ በተመለከተ ሀገራዊ ንስሃ መልእእክት (በ121 ሰዎች)፣ የክርስትና ማንነት (በ46 ሰዎች)፣ በድምሩ የ290 ሰዎች እይታ ያገኘ ሲሆን፣ 15 ሰዎች ተጨማሪ ሥራ በመሥራታቸዉ ድምሩን 305 ያደርሰዋል። በጠቅላላ ድምር የ 1232 ሰዎች እይታ አግኝቷል ማለት ነዉ።

**5.2 በፓ/ር ጌታቸዉ በቀለ (መገናኛ ሙሉ ወንጌል)** በአማርኛ በዩቲዩብ 1-10 ክፍሎች የተዘጋጁ የደቀመዝሙር ትምህርቶች፣ በድጋሚም ሆነ እንደ አዲስ፣ የጎበኙ ሰዎች ቁጥር 889 ሲሆን፣ ለሌሎች መልሰዉ በማጋራት ተጨማሪ ሥራ የሠሩ 38 በመሆናቸዉ፣ በድምሩ የ927 እይታ አግኝቷል።

## ክፍል ስድስት - እአአ 2023 የሂሳብ እንቅስቃሴና እአአ የ2024 በጀት ዕቅድ

እአአ 2023 (ጃኑዋሪ እስከ ዲሴምበር) ለዓመቱ ተይዞ የነበረው በጀት **ብር** 698,740.00 **(**ስድስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ፣ ሰባት መቶ አርባ ብር) የነበረ ሲሆን፣ አጠቃላይ ወጪ ብር 304,431.21 (ሶስት መቶ አራት ሺህ፣ አራት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም) ነበር፤ ይህ በኦዲቴር የተረጋገጠ ነዉ።

**እአአ ለ2024 ዓም** ለአገልግሎቱ **የተያዘዉና** በቦርድ ታይቶና በጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀዉ ብር 773,860.00 ነዉ። ለተፈጻሚነቱ እንፀልይ፣ ጌታም ይረዳናል። አሜ! አሜን! አሜን!

**ማጠቃለያ ፣** ለዚህ አገልግሎት መሳካት ምክንያት፣ ከሁሉ በላይ ሊመሰገንና ከፍ ሊል የሚገባዉ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነዉ። በማይመቹ አካባቢዎች ስንንቀሳቀስ ሁሉ ጥበቃዉን ያበዛልን እርሱ ነዉና ክብር ለርሱ ይሁን። አገልግሎቱ በእግሩ እንዲቆምና ወደፊት እንዲሮጥ፣ አገልግሎቱን በመምራት በትጋት ለተንቀሳቀሳችሁ ቦርድ አባላት ፤ በቋሚነት ገንዘባችሁን በመለገስ ለተጋቻሁ ደጋፊዎች፤ በበጎ ፈቃደኝነት ጊዜያችሁን ፣ ጉልበታችሁን በመስጠት ላገለገላችሁ ወገኖች ፣ በራችሁን በመክፈት በትብብር እንዲሠራ ለፈቀዳችሁ፣ በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጪ ላላችሁ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወጣቶች፣ ጥልቅ ምስጋናና ዕዉቅና በዚህ ሪፖርት አማካይነት ተሰጥቶአችኋል።

እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና። ዕብራውያን 6:10፤

***እርስዎና ቤተሰብዎም ለዚህ አገልግሎት መሳካት የበኩሎዎን ድርሻ ስላበረከቱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ እንላለን።***

**መጨረሻ**